# በአለም አቀፍ የቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን እና ዩኔስኮ ትብብር የተዘጋጀ የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ማኒፌስቶ

በዚህ የመረጃና የዕውቀት ዘመን ውጤታማ ሆኖ ለመዝለቅ የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎችንና ጠቃሚ ሃሳቦችን በማቅረብ ያገለግላሉ:: የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ተማሪዎች በህይወት ዘመናቸው የማያቋርጥ የመማር ችሎታ እንዲያዳብሩና ሃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች እንዲሆኑ የሚረዳቸውን ዕውቀት የሚገበዩባቸው ሥፍራዎች ናቸው::

## የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ተልዕኮ

የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ሁሉም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት የሰላ የአስተሳሰብ ችሎታ እንዲኖራቸውና መረጃዎችን በማናቸውም መልኩ በውጤታማነት መጠቀም እንዲችሉ ለመርዳት የመማሪያ መርጃ አገልግሎቶች፣ መፃሕፍትና ሌሎች መጠቀሚያዎች የሚቀርቡባቸው ናቸው:: የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ከአጠቃላዩ የቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ ጥምረት ጋር በዩኔስኮ የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ማኒፌስቶ መመሪያዎች መሠረት ግንኙነት ያደርጋሉ::

መፃሕፍትና ሌሎች የመረጃ ምንጮች ከልብ ወለድ እስከ ጥናታዊ መረጃዎች፣ ከሕትመት እስከ ኤሌክትሮኒክስ ያሉት በቤተ-መፃሕፍቱም ውስጥ ይሁን ከዚህ ውጭ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የቤተ-መፃሕፍቱ ሠራተኞች ድጋፍ ይሰጣሉ:: በቤተ-መፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት ስብስቦች የመማሪያ መፃሕፍትን፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎችንና ዘዴዎችን በመደገፍና በማዳበር ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው::

የቤተ-መፃሕፍት ሠራተኞችና መምህራን በመደጋገፍና በመተባበር በቅንጅት በሚሰሩበት ወቅት ተማሪዎች መሃይምነትን በማጥፋት፣ በንባብ፣ በመማርና እንዲሁም በመፍትሔ ሰጭነትና መረጃዎችንና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ረገድ እጅግ ውጤታማ እንደሚሆኑ ታውቋል::

የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት አገልግሎት ለሁሉም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት የዕድሜ፣ የዘር፣ የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የብሔር፣ የቋንቋ ወይም ማህበረሰባዊ ደረጃን የተመረኮዘ ልዩነት ሳይደረግ በእኩልነት ሊሰጥ ይገባል:: በቤተ-መፃሕፍቱ መደበኛ አገልግሎቶች ወይም መሣሪያዎች መጠቀም ለማይችሉ የተለየ አገልግሎት ወይም መሣሪያ ሊቀርብላቸው ያስፈልጋል::

በቤተ-መፃሕፍቱ አገልግሎቶችና ስብስቦች መጠቀም መቻልን በተመለከተ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብትና ነፃነት አለም አቀፍ ድንጋጌ መሠረት መፈፀም የሚገባው ሲሆን አገልግሎቶቹና ስብስቦቹ ከማናቸውም ዓይነት የርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ ወይም ሃይማኖታዊ ቁጥጥር እና የንግድ ጫና ነፃ መሆን ይኖርባቸዋል::

## የገቢ ምንጭ፣ ሕጐች እና የግንኙነት ሰንሰለቶች

መሃይምነትን የማጥፋት፣ የትምህርት፣ የመረጃ አቅርቦት ወይም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ዕድገትን አስመልክቶ የረጅም ጊዜ ዕቅድ በሚነደፍበት ወቅት የትምህርት ቤት ቤተ-መፃሕፍት በዚህ ዕቅድ ውስጥ ሊካተቱ ይገባል:: ቤተ-መፃሕፍቱ የአካባቢ፣ የክልል እና የብሔራዊ ባለሥልጣናት ሃላፊነት እንደመሆናቸውም ለእነርሱ ተብሎ በወጣ ልዩ ሕግና ፖሊሲ ሊደገፉ ይገባል:: የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ለሠራተኞች ሥልጠና፣ ለዕቃ አቅርቦት እና ለቴክኖሎጂዎችና ሌሎች መሣሪያዎች በቂና የማይቋረጥ በጀት መመደብ ያስፈልጋቸዋል:: አገልግሎታቸውንም ከክፍያ ነፃ ማድረግ ያስፈልጋል::

በአካባቢ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ የቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ ጥምረት ውስጥ የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት እጅግ አስፈላጊ አካል ናቸው:: የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ከሌላ ዓይነት ቤተ-መፃሕፍት ለምሳሌ ከሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ጋር የመጠቀሚያ ቦታን ወይም ስብስቦችን በጋራ በሚጠቀሙበት ወቅት የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ልዩ ዓላማዎች በግልጽ ሊታወቁና ሊጠበቁ ይገባል::

## የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ግብ

የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት የመማርና ማስተማር ሂደት አንድ አካል ናቸው::
ከዚህ የሚከተሉት መሃይምነትን ለማጥፋት፣ ለመረጃ ዕውቀት፣ ለመማር ማስተማር እና ለባሕል ዕድገት አስፈላጊ ሲሆኑ የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ዋነኛ አገልግሎቶችም ናቸው::

- በትምህርት ቤቱ ዓላማና የትምህርት ዕቅድ ላይ በተመለከተው መሠረት የትምህርቱን ግብ መደገፍና ማሳደግ፣
- የማንበብና የመማርን ልምድና ፍቅር እንዲሁም በሕይወት ዘመን ሁሉ የማይቋረጥ የቤተ-መፃሕፍት ተጠቃሚነትን በሕፃናት ወስጥ ማስረጽና ማሳደግ፣
- መረጃን ለዕውቀት፣ ለግንዛቤ፣ ለጥልቅ እሳቤ ወይም ለመዝናኛ ማዘጋጀትና መጠቀም የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የመገናኛ ዘዴዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተማሪዎች በማናቸውም መልኩ የሚገኙ መረጃዎችን መመርመርና መጠቀም ይችሉ ዘንድ ትምህርት እንዲያገኙና ልምምድ እንዲያደርጉ መደገፍ፣
- ባሕላዊና ማህበራዊ ትውውቅና መተሳሰብን የሚያበረታቱ የተለያዩ ዝግጅቶችን ማቅረብ፤
- የትምህርት ቤቱ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ከተማሪዎች፣ ከመምህራን፣ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ከወላጆች ጋር በመተባበር መሥራት፤
- ተማሪዎች ከተለያዩ ሃሳቦች፣ ልምዶችና አስተሳሰቦች ጋር እንዲተዋወቁ ከአካባቢ፣ ከክልል፣ ከብሔራዊና አለም አቀፍ የዕውቀት ክምችቶችና ዕድሎች ጋር የሚገናኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- ሃላፊነት የሚሰማቸውን ዜጎች ለመፍጠርና በዲሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ በብቃት መሳተፍ ይቻል ዘንድ ምሁራዊ ነፃነትና መረጃዎችን የማግኘት መብት እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ማስተማር፤
- የማንበብን ልምድና በትምህርት ቤቶቹ ቤተ-መፃሕፍት ውስጥ የሚገኙትን ስብሰቦችና አገልግሎቶች ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ከዚያም ውጪ ለሚገኙ ማስተዋወቅ፤

የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት እነዚህን ተግባሮች ሊያከናውኑ የሚችሉት አግባብ ያላቸውን ፖሊሲዎችና አገልግሎቶችን በማዳበር፣ ስብስቦችን በጥራት በመምረጥና በመያዝ፣ ተገቢ የመረጃ ምንጮችን ማግኘት ይቻል ዘንድ በቤተ-መፃሕፍቱ የመጠቀሚያ መንገዶችን ሁሉ ክፍት በማድረግና በማመቻቸት፣ የተለያዩ የዕውቀት መርጃ ዘዴዎችን በማቅረብ እና የሰለጠኑ የቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎች በማሰማራት ነው።

## የቤተ-መፃሕፍቱ ሠራተኞች

አንድ የትምህርት ቤት ቤተ-መፃሕፍት ባለሙያ በተቻለ አቅም በበቂ የድጋፍ ሠራተኞች በመታገዝና ከሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት ጋር ተባብሮ በመሥራት እንዲሁም ከህዝብ ቤተ-መፃሕፍትና ከሌሎች ጋር ግንኙነት በማድረግ የትምህርት ቤቱን ቤተ-መፃሕፍት በዕቅድ ለመምራትና ለማስተዳደር ሃላፊነት የተጣለበት በሙያው የዳበረ ዕውቀት ያለው ሠራተኛ ነው።

እንደየሁኔታው እየታየ የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎች ውጤታማ የሆኑ የትምህርት ቤት ቤተ-መፃሕፍት አገልግሎቶችን ማለትም የመጠቀሚያ ስብስቦችን፣ ቤተ-መፃሕፍቱን እና የመረጃ አስተዳደርና ትምህርትን ለማዳበርና ለመምራት ይችሉ ዘንድ የሚያስፈልጋቸው የዕውቀት ወይም የትምህርት መስኮች አሉ።

መምህራንና ተማሪዎች የተለያየ የመረጃ አያያዝ ዕውቀት እንዲኖራቸው ለማስተማርና ለማቀድ የትምህርት ቤቶች ቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎች ብቁ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ስለዚህ ባለማቋረጥ ሙያዊ ስልጠናዎችን እንዲከታተሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የሥራ አፈፃፀምና አመራር

ተጠያቂነት ያለውና ውጤታማ የሆነ ሥራ ለመሥራት:-

- የትምህርት ቤት ቤተ-መፃሕፍት አገልግሎት ፖሊሲ ግቦችን፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ሁኔታዎችንና አገልግሎቶችን ከትምህርት ቤቱ የትምህርት ዕቅድ አንፃር መቅረጽ ይኖርበታል፡፡
- የትምህርት ቤቱ ቤተ-መፃሕፍት ሙያው የሚጠይቀውን ደረጃ ጠብቆ መደራጀት የሚኖርበት ሲሆን ይህም በዘላቂነት ሊጠበቅ ይገባል፤
- የትምህርት ቤቱ ቤተ-መፃሕፍት ለሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት ክፍት መሆን የሚኖርበት ሲሆን አገልግሎቱም የአካባቢውን ህብረተሰብ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፤
- ከመምህራን፣ ከከፍተኛ የትምህርት ቤቱ አመራር፣ ከአስተዳዳሪዎች፣ ከወላጆችና ከሌሎች የቤተ-መፃሕፍትና የመረጃ ባለሙያዎች እንዲሁም ከማህበረሰባዊ ቡድኖች ጋር ያለው ትብብር ሊበረታታ ይገባል፡፡

## ማኒፌስቶውን ወደ ተግባር ስለመለወጥ

መንግሥታት የትምህርት ጉዳይ በሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቻቸው በኩል የዚህን ማኒፌስቶ መርሆዎች ወደ ተግባር ለመለወጥ የረጅም ጊዜ ዕቅዶችንና ፖሊሲዎችን እንዲያወጡ ይጠየቃሉ፡፡ ዕቅዶቹም ማኒፌስቶውን በማስፋፋት ረገድ የቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎችንና መምህራንን በአጭርና እንዲሁም በተከታታይ የስልጠና ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ ማድረግን ሊያካትቱ ይገባል፡፡